# ዘላቂ ልማትና መልካም አስተዳደር

## ክፍል አንድ


## በሽር ሁሴን 12-19-14


በኢትዮጵያ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ከተዘረጋ ሁለት አሥርት ዓመታት አልፈዋል። በአገሪቱ የተፈጠረው ምቹና ሰፊ የፖለቲካ ምህዳር በመጠቀምም ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ተመሥርተው የፖለቲካ አጀንዳቸውን ለማሳካት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ ። ባለፉት ሃያ ዓመታት በየአምስት ዓመቱ በተካሄዱ አራት ምርጫዎች ላይ እነዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች የነበራቸው ተሳትፎ የጎላ እንደነበር እሙን ነው።

ይሁንና አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች የአገሪቱ ሕገመንግስት በሚፈቅደው መሰረት የህዝቡን ይሁንታና ድጋፍ ለማግኘት ጥረት እያደረጉ እንዳሉ ቢታወቅም በተቃራኒው አንዳንድ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ደግሞ በሕጋዊ የፖለቲካ ድርጅት ስም ሕገመንግስቱን ሲተላለፉ ይታያሉ።

የዜጎችን መብትና እኩልነት ያረጋገጠውና ዜጎች በፈለጉት የፖለቲካ ድርጅት ያለምንም ተጽእኖ ተደራጅተው እንዲሳተፉ ሙሉ ነጻነታቸውን ያጎናጸፈን የአገሪቱ የበላይ ሕግ የሆነው ሕገ መንግሥት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ለመናድ ያለመ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ይስተዋላሉ ።

ህልውናው የፈጠረላቸውንና በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ ያስቻላቸውን የአገሪቱን ሕገ መንግሥት አክብረው መንቀሳቀስና የፖለቲካ አጀንዳቸውን በሕዝብ በማስረፅ በምርጫ አሸንፈው ወደ ሃላፊነት መምጣት የሚያስችላቸውን ቀና መንገድ ከመከተል ይልቅ ይህ ነው የሚባል አጀንዳ ሳይዙና በሕዝቡ መካከል ሁከትና ትርምስን በመፍጠር በግርግር ለመጠቀም አልመው በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሕገ መንግሥቱን ሲተላለፉ ይስተዋላሉ ።

በቀደሙት ዓመታት በአገራችን የተቃዋሚ ነየፖለቲካ ድርጅቶች የሚያራምዷቸው ሕጋዊነት የጎደላቸው ተግባራት በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ጥያቄ ያስነሱ እንደነበሩ ይታወቃል። በተለይም አገራችን የሚታካሂዳቸውን ትላልቅቅ የልማት ፕሮጀክቶችን በማጣጣልና ተገቢ ያልሆነና የተዛቡ አስተያየቶችን በመስጠት የአገሪቱን ብሄራዊ ድህነንት ሊፈታተኑ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎችን በመቃወምና ከአገሪቱ የውጭ ጠላቶች ጋር በማበርና በመተጋገዝ የተሳሳተ መንገድ ሲሄዱ መስተዋላቸው ይታወቃል።

የኪራይሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ መሰረት በመናድ የልማታዊ ኢኮኖሚን ለማረጋገጥ እየተደረገ ያለው ሁለንተናዊ ጥረት ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል። በገጠር የነበረው የኪራይሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ መሰረት ለመናድ የተለያዩ እርምጃዎች መወሰዳቸው ይታወቃል።

የኢህአዴግ መንግስት ሰው በላውን የደርግ መንግስት ገርስሶ አገሪቱን በተቆጣጠረበት ወቅት በከተማም ሆነ በገጠር ኪራይሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ የተንሰራፋበትና ልማታዊ አስተሳሰብ የሚባል ነገር ያልነበረበት ሁኔታ ነበር። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በገጠር የመሬት ክፍፍል የተደረገና አርሶ አደሩ መሬት ያገኘበት ሁኔታ የነበረ ቢሆንም አንዳንድ የፍትሃዊነት ችግሮችን የማስተካከል ስራ በመስራትና በአንዳንድ አካባቢ የነበሩ በተገቢው መልክ ክፍፍሉ ያልተደረገባቸው አካባቢዎች ብቻ የማስተካከያ ስራዎችን በመስራት ባለበት እንዲሄድ የተደረገበት ሁኔታ ነበር።

ከመሬት ይዞታ ጋር ተያይዞ በአርሶ አደሩ የነበረ ኋላ ቀር አስተሳሰብን ለመቅረፍ ያላሳለሰ ጥረት ተደርጓል። አርሶ አደሩ በላቡ ሰርቶ ጥሮና ግሮ አኗኗሩን መቀየር የሚችልበትን ሁኔታ በማመቻቸትና የተለያዩ ግብአቶችን በማቅረብ የአርሶ አደሩን ምርታማነት ለማሳደግ የተሰራው ስራ በገጠር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ብሎም በአገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ዋስትና ለማረጋገጥ የጎላ ድርሻው መወጣት እየቻለ

ያለበት ሁኔታ መፈጠሩም የኪራይሰብሳቢነት ምንጮችን ለመዝጋት የተደረገው ጥረት አጓጉ ሚና እንደነበረው ለማየት ይቻላል።

አርሶ አደሩ በተሰጠው የእርሻ ቦታ ላይ የራሱንና የቤተሰቡን ላብ አፍስሶና በመንግስት ከሚመደቡ ባለሙያዎች የምክር አገልግሎት እያገኘ ሰርቶ ከድህነት መላቀቅ የሚቻል መሆኑን በተግባር መገንዘብ በመቻሉ ልማታዊነቱ እያደገ በመጣ ቁጥር በገጠር የኪራይሰብሳቢነት መሰረት እየተናደ መምጣቱን መረጃዎች ያሳያሉ።

በአሁኑ ወቅት ከአረሶአደርነት ወደ ኢንቬስትርነት የተቀየሩ አርሶአደሮች ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። በገጠር ሞዴል አርሶ አደሮች ሌላውን እየመሩና በአንድ ለአምስት አደረጃጀት በመሰባሰብ ድህነትን ለመዋጋት ቆርጠው ተነስተው ልማታቸውን እያረጋገጡ ያሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህ ደግሞ ለኪራይሰብሳቢነት መሰረት መናድ ሌላው ምክንያት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

በዚህ መልክ ልማታዊነት እየተረጋገጠና ኪራይ ሰብሳቢነትን ነቅሎ ለመጣል እየተናነቀ ይገኛል። በከተማም በተመሳሳይ መልኩ የኪራይሰብሳቢነትን የበላይነት ለመድፈቅና ልማታዊነትን ለማንገስ ቀላል የማይባል ስራ እየተከናወነ ይገኛል።

እንደ መሬት፣ የመንግስት ግዥ፣ ግብርና ንግድ የመሰሳሰሉ ለኪራይሰብሳቢነት ዋና ምንጭ ተደርገው የሚወሰዱ ዘርፎች ተለይተው በሰፊው እየተሰራበት ይገኛል። ኪራይሰብሳቢነትን ለመዋጋት ጥረት እየተደረገ ነው። ኪራይሰብሳቢነትን ለመዋጋትና ልማታዊነትን ለማጠናከር መልካም አስተዳደር ማስፈን አንዱ ነው።

መልካም አስተዳደርን ማስፈን የኪራይሰብሳቢነትን አንድ መንገድ መዝጋትና የአገሪቱን ልማት ማፋጠን መሆኑን የተገነዘበው የኢትዮጵያ መንግስት ለመልካም አስተዳደር መስፈን የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል። ሆኖም ግን መልካም አስተዳደርን የማስፈን ተግባር የአንድ ጀምበር ተግባር አይደለም። ጊዜን የሚጠይቅና በሂደቶች የሚከወን እንደሆነ ይታወቃል።

በአገሪቱ የፖለቲካል-ኢኮኖሚ ዕድገት የሚወሰነውንና በየጊዜው መሻሻል እያሳየ የሚገኘውን የመልካም አስተዳደር ክንዋኔን በአንድ ጀምበር እንዲጠናቀቅ የሚፈልጉ አንዳንድ ወገኖች መልካም አስተዳድር የለም እያሉ በተደጋጋሚ ከማስተጋባትም ባሻገር በየጊዜው የተለያዩ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ እሳቤዎችን በማምጣትና በአገሪቱ የተረጋገጠውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በማያግዝበና ለማጠናከር በማይጠቅም መልክ ሲንቀሳቀሱ ይስተዋላል።

የመልካም አስተዳደርን ምንነት በመተንተን በተቃዋሚዎች በኩል ባለማወቅም ይሁን በፍላጎ "አቡነ ዘበሰማያት" ይመስል ጧትና ማታ የሚደገመው የመልካም አስተዳደር ጉዳይ እነሱ ስለዘመሩ ሳይሆን መንግስት በአገሪቱ መልካም አስተዳደርን የማስፈን ተግባር ልማታዊ የበላይነትን ለማረጋገጥ ከሚኖረው ሚናና የህዝብን ጥያቄ ከመመለስ አንጻር ቀዳሚ አጀንዳውን አድርጎ የያዘው ጉዳይ በመሆኑ ነው። መልካም አስተዳደር የህልውና ጉዳይ ነው። ምክንያቱም መልካም አስተዳደርን ማስፈን ካልተቻላ ኪራሰብሳቢነትን ደፍቆ ልማታዊነትን ማረጋገጥ የራሱ አሉታዊ ተጽእኖ ስላለው።

የመልካም አስተዳደር ትግበራ የሀገራችንን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዕለታዊ ህይወት በቀጥታ የሚነካ በመሆኑም፤ በአተገባበሩ ዙሪያ ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ መጠነ ሰፊ ተግባራዊ ክንዋኔዎች ተደርገው አበረታች ለውጦች እየተመዘገቡ መጥተዋል። ይሁንና አንዳንድ በተቃውሞው ጎራ የተሰለፉ ወገኖች የሀገሪቱ መንግስትና ገዥው ፓርቲ ያከናወኑትን ተግባራት ሳይገነዘቡ በደፈና ተቃውሞ እየተመሩ 'መልካም አስተዳደርን አሁኑኑ ውለዱ' በማለት በየሚዲያው የጥላቻ ዲስኩር ሲያሰሙ ይሰተዋላል።

እነዚህ ወገኖች በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መንግስትንና ገዥውን ፓርቲ ለማብጠልጠል ሁሉንም አማራጮች አሟጠው ለመጠቀም የሚያደርጉት አግባብነት የሌለው የመከራከሪያ ነጥብ 'እዚህ ሀገር አልነበሩም እንዴ?' የሚያሰኝ ነው። የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ ማንኛውም ሰው የመሰለውን ሃሳብ የመግለፅ ህገ-መንግስታዊ መብት እንዳለው ይገነዘባል።

ይሁንና ሃቁን ላለማየት ዓይናቸውን በጥቁር መሃረብ ሆን ብለው በመሸፈን ለማጥላላት ተብለው የሚሰነዘሩ አስተያየቶች ነባራዊ ዕውነታውን የሚመለከቱ አይደሉምና ተገቢ ምላሽ እንደሚያስፈልጋቸውም ያምናል። እናም 'ዕውን የመልካም አስተዳደር በአንድ ጀምበር ገቢራዊ ይሆናልን?'

የሚል ጥያቄ በማንሳት፣ በሀገራችን በመስኩ እየተከናወኑ ያሉትን አተገባበሮችንና የተገኙትን ውጤቶች እየጨለፍን እንመለከታለን። ይህም አንዳችም የነጠረ ፖሊሲና ስትራቴጂ ሳይኖራቸው በጭፍን ተቃዋሚነት የተሰለፉ ተቃዋሚ ተብዬዎችን የፀረ-ዴሞክራሲ እሳቤዎችን በገሃድ ለማየት ያስችለናል።

እንደሚታወቀው መልካም አስተዳደር የዴሞክራሲ አካልና መሠረት ነው። ስለሆነም መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባህል ግንባታን በግብነት አስቀምጦ መረባረብ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ አያጠያይቅም። ታዲያ ይህን ዕውነታ በውል የተገነዘበው የኢትዮጵያ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስትም፣ ሃሳቡን ወደ ድርጊት ለመለወጥ በጥረት የታገዙ ጠንካራ እንቅስቃሴዎችን ከጀመረ ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ አስቆጥሯል።

እስቲ በቅድሚያ ስለ መልካም አስተዳደር የሂደት ግንባታ እናውጋ። በዓለም ባንክ ብያኔ መሠረት መልካም አስተዳደር ማለት ሊተነበይ የሚችልና በነጠረ ፖሊሲ አወጣጥ የተካነ እንዲሁም በሙያው ስነ-ምግባር የሚታገዝና በሚወስዳቸው እርምጃዎች ተጠያቂ ሊሆን የሚችል መንግስትና በመንግስታዊ ጉዳዮችም በንቃት የሚሳተፍ ህብረተሰብ ያለበት ሆኖ፣ ሁሉም አካላት በህግ የበላይነት አምነው የሚንቀሳቀሱበት ስርዓት ነው።

እርግጥ በዚህ ትርጓሜ ውስጥ ያሉት አባባሎች ለመልካም አስተዳደር ጠቃሚ መሆናቸው አያጠያይቅም። ይሁን እንጂ አባባሎቹ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታቸውን ከዛሬ ሁለት መቶ ዓመት በፊት መስርተው በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሰዋል የሚባሉት ምዕራባውያንም እንኳን ቢሆኑ ሙሉ ለሙሉ ገቢራዊ

አድርገዋቸዋል ብሎ ለመናገር አያስደፍርም። ከእኛ ሀገር የሃያ ዓመት ታዳጊ ዴሞክራሲ አኳያም፤ ተግባሩ ተቃዋሚዎች "መንግስት ባለፉት ዓመታት መልካም አስተዳደርን አላሰፈነም" እያሉ እንደሚያስወሩት ሳይሆን የራሱን ሂደት ጠብቆ በጊዜ ዑደት ውስጥ የሚገነባ ሆኖ እናገኘዋለን።

እናም ከመልካም አስተዳደር አኳያ በመጀመሪያ መታወቅ ያለበት ጉዳይ፤ ተግባሩ በሂደት እንጂ በአንድ ጀምበር የሚመጣ አለመሆኑን ነው። ምዕራባውያንም ቢሆኑ ዛሬ ለደረሱበት የመልካም አስተዳደር ተግባር (ለዚያውም ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ባላደረጉበት ሁኔታ) ረጅም ጊዜ የወሰደባቸው መሆኑን መገንዘብ ያሻል። በመሆኑም እንደ ኢትዮጵያ ያለ ጀማሪ የዴሞራሲያዊ ስርዓት ባህል ግንባታ አራማጅ ሀገር፤ ተግባሩን "በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ካላመጣች" ብሎ በጭፍን መሞገት ለሰሚው ግራ የሚያጋባ ይሆናል።

ስለሆነም በቅንጭብጫቢ ኒዮ-ሊበራል እሳቤ ከወዲያ ወዲህ የሚላጉት ተቃዋሚ ተብዬዎችም አድማጭ እናገኛለን በማለት "መንግስት መልካም አስተዳደርን ማስፈን ተስኖታል" እያሉ የሚያላዝኑት የአላዋቂነት ድርሰት ከዚህ አኳያ መታየት ያለበት ይመስለኛል። ተግባሩን ከሰማይ በአንድ ቀን እንሚወርድ መና ቆጥረው 'የግድ አሁኑኑ መፈፀም አለበት' ብሎ ማሰብ ከዕውቀት አጠርነት በስተቀር ሌላ ስያሜ የሚያሰጥ አይመስለኝም–"አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል" እንዲሉ።

ታዲያ እዚህ ላይ ውድ አንባቢዎቼ እንዲገነዘቡልኝ የምሻው ጉዳይ አለ። ይኸውም መንግስትና ገዥው ፖርቲ መልካም አስተዳደር ጊዜ ስለሚወስድ ተግባሩን ላለማከናወን እጃቸውን አጣጥፈው አለመቀመጣቸውን ነው። ይልቁንም ላለፉት 23 ዓመታት መልካም አስተዳደር በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባህል ግንባታ ውስጥ ስር እንዲሰድ ዘርፈ ብዙ ጥረት አድርገዋል። በመሆኑም በተቃዋሚዎቹ ለመቃወም ብቻ የሚሰነዘሩ ሃሳቦች እነዚህን ጥረቶች የሚወክሉ አይደሉም።

ጥረቶቹ እየታወቁ "ዓይኔን ግንባር ያድርገው" በሚል የተለመደ የተቃውሞ ብሂል ለማጣጣል ተብለው ቀርበው ከሆነም፤ አስተሳሰቦቹ ተገቢ ያልሆኑ ብቻ ሳይሆኑ

ዕውነታውን የሚያውቀውን ህዝብ በመናቅ ሀገራዊ ሃላፊነት በጎደለው ሁኔታ የተሰነዘሩ ናቸው ለማለት ይቻላል።

ማንም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው ባለፉት 23 ዓመታት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል፤ አጥጋቢ ውጤቶችም ተገኝተዋል። የሀገራችን ዴሞክራሲ ስር መስደድ ይችል ዘንድ በሁሉም ደረጃዎች የዴሞክራሲ ተቋማት እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ፣ የዳበረ የፍትህ ስርዓት እንዲገነባ፣ የህዝቡ ዴሞክራሲያዊ ባህል እንዲጎለብት፣ በየደረጃው ባሉ የመንግስት አካላት ውስጥ የግልፅነት፣ የተጠያቂነትና የህዝብ አገልጋይነት መርህ እንዲሰፍንና የተግባር መመሪያ እንዲሆን ብሎም በሁሉም መስኮች የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ...ወዘተ ብርቱ ጥረት ተደርጓል።

ይሁንና የተቃውሞው ጎራ ግን የተከናወኑትን በጎ ተግባሮች ግምት ውሰጥ ሳያስገባ በጭፍን የህግ አስፈፃሚውን አካል በደፈናው ለማውገዝ መሯሯጡ ከትዝብት ውጪ የሚያተርፍለት አንዳችም ነገር ያለ አይመስለኝም። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደቱን አንድም ስንዝር ፈቅ ሊያደርገው ስለማይችል ነው። ለምን ቢባል፤ ጭፍን ጥላቻ ፀረ-ዴሞክራሲያዊነትን እንጂ ዴሞክራሲያዊነትን ሊወልድ ስለማይችል ነው።

የሀገራችን የህግ አስፈፃሚ አካል ተቃዋሚዎቹ እንደሚያስደምጡን የጥላቻ አሉባልታ ዲስኩር ሳይሆን፤ በህግና በህግ ማዕቀፍ ውስጥ ብቻ የሚመራና የሚሰራ ነው። በመሆኑም አባሎቻቸው በወንጀል ተጠርጥረው በህግ ጥላ ስር ሲውሉ "የህግ የበላይነት የለም" እያሉ የሚያላዝኑት ተቃዋሚዎች ይህን ሃቅ ሊረዱት ይገባል። ምክንያቱም በህግ ጥላ ሰር የሚገኝ ማንኛውም ታራሚ ህጉ የሚፈቅድለትን ነገሮች ሁሉ ከማከናወን የሚያግደው አንዳችም ነገር ስለሌለ ነው።

የመልካም አስተዳደር ቁልፍ መርህ የሆነው የህግ የበላይነት ያለምንም መሸራረፍ ገቢራዊ ለማድረግ ታስቦ የሚከናወን መሆኑን ግንዛቤ መያዝ ያሻል ። በመሆኑም

ተቃዋሚዎቹ ለአንድ ወይም ለሁለት አባሎቻቸው ተብሎ የሚቀለበስ የህግ የበላይነት ሊኖር እንደማይችል ማወቅ ያለባቸው ይመስለኛል።

እንደሚታወቀው በፍርድ ቤት በተያዘ ጉዳይ አስፈፃሚው አካል በማንኛውም መስፈርት ጣልቃ የሚገባበት ሁኔታ የለም፤ ሊኖርም አይችልም። ምናልባትም እንዲህ ዓይነቱ ጣልቃ ገብነት ተቃዋሚዎቹ በሚያራምዱት ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ውስጥ ገቢራዊ ሊሆን ይችላል።

ሀገራችን በተያያዘችው ደዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ ግን እንኳንስ ሃሳቡን ገቢራዊ ማድረግ ቀርቶ ማሰብም አይቻልም። ምክንያቱም የመንግስት ፖሊሲና አሰራሮች ለጥቂት ግለሰቦች አሊያም ሌላውን ወገን ላለማስከፋት ሲባል የሚለወጡ ባለመሆናቸው ነው።

እርግጥ የመንግስት አካላትና ሃላፊዎች ፖሊሲዎቻቸውን በየቀኑ የሚቀያይሩ ከሆነ ህዝብ የጣለባቸውን አደራ ይወጣሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ለነገ ብለው የሚያቅዱት ነገርም አይኖርም። ዳሩ ግን የህግ የበላይነት ሲኖር፤ ህጎች በምክር ቤት ውይይት አማካኝነት ፀድቀው ካልሆነ በስተቀር በየቀኑ አይቀያየሩም። ማንኛውም ሰው በእነዚህ ህጎች ስር ሆኖ ስለሚሰራና ህጎቹንም የሚተላለፍ ስለሚቀጣ ከህግ ውጪ እንዳሻው የሚሆን ዜጋ ሊኖር አይችልም። በመሆኑም የህግ ልዕልና ይረጋገጣል ማለት ነው።

ታዲያ በአንድ ወገን "አስፈፃሚው አካል በህግ የበላይነት ውስጥ ጣልቃ መግባት የለበትም" እያሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ "መንግስት አባሎቻችንን እያሰረ የህግ የበላይነትን አያከብርም" በማለት እርስ በእርሱ የሚጣረስና ግራ የገባው ፖለቲካን የሚያራምዱት ተቃዋሚዎች ምን እያሉን ይሆን?፣ እንዲህ ዓይነቱ እርስ በእርሱ የሚጋጭ እሳቤስ በተቃዋሚኛ ከቶ ምን ማለት ይሆን?፣ ለመሆኑስ በተቃዋሚኛ የህግ የበላይነት ማለት መንግስት ሲያሻው ጣልቃ የሚገባበት፤ በል ሲለው ደግሞ "አልገባም" የሚልበት ተግባር ነውን?

እርግጥ የእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ከተቃዋሚዎች አኳያ ምን እንደሆነ ባላውቅም፣ ከዴሞክራሲ አሰራር አንፃር ግን ምላሹ "አይደለም" የሚል ነው። በመሆኑም የህግ የበላይነት በታወቀ የህግ ማዕቀፍ ውስጥ የሚሰራበት መሰረታዊ የዴሞክራሲ መርህ መሆኑን ግንዛቤ መያዝ ያሻል።

የህግ የበላይነት በየጊዜው በመንግስት ወይም በግለሰቦች የሚጣስ ከሆነ፣ ጅምር ዴሞክራሲያችን አደጋ ላይ መውደቁ ስለማይቀር ነው። ዳሩ ግን ከተቃዋሚዎቹ በስተቀር ህዝቡም ሆነ መንግሰት ታዳጊው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲደናቀፍ አይፈልጉም።

ዴሞክራሲያዊ አሰራርን የኢ-ዴሞክራሲያዊ ካባ ደርበው የሚንቀሳቀሱት ተቃዋሚዎች ይህ በህዝቡ የማይደገፍ እኩይ ሴራቸው "ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ" እንዲሉት ዓይነት መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም ህዝብን እንደ ህዝብ የሚንቅ ማንኛውም አካል የመጨረሻ ዕጣ ፈንታው "ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ..." ተብሎ መወርወሩ አይቀርምና። አንድ ዕወነታን ማንሳት ወደድኩ። ይኸውም መልካም አስተዳደር የህዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ካልታከለበት በመንግስት ጥረት ብቻ ተግባራዊ ሊሆን የማይችል መሆኑ ነው። ማንኛውም ህዝብ ያልተሳተፈበት ጉዳይ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልምና።

በመሆኑም በመንግስት በኩል መልካም አስተዳደርን ዕውን ለማድረግ እየተከናወኑ ያሉና በሂደት የሚከናወኑት ቁርጠኛ ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው፣ መላው ህዝብም ዛሬም እንደ ትላንቱ ለተግባራዊነቱ መረባረብ ይኖርበታል። በተለይም ቁልፍ የዴሞክራሲ ማስፈኛ ተቋማት በሚባሉት እንደ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ዓይነቶችን በአግባቡ በመጠቀምና የሚፈጠሩ ችግሮችን ተከታትሎ በማሳወቅ ለመልካም አስተዳደር እመርታ መትጋት ከማንኛውም ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር ነው።መንግስት ምንም እንኳን ግዴታው ቢሆንም ህገ-መንግስቱ በሚያዘው መሰረት ብሎም ራሱም ለዴሞክራሲ ስር መስደድ ካለው ቀናዒ ፍላጎት በመነሳት፣ መልካም

አስተዳደርን ለማስፈንና የዜጎች አቤቱታ የሚደመጥበት እንዲሁም ተገቢው ምላሽ የሚሰጥበት የእንባ ጠባቂ ተቋምን አቋቁሟል።